22140009

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A: LITERATURE – HIGHER LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A : LITTÉRATURE – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A: LITERATURA – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 1**

Friday 9 May 2014 (morning)
Vendredi 9 mai 2014 (matin)
Viernes 9 de mayo de 2014 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a literary commentary on one passage only.
- The maximum mark for this examination paper is *[20 marks]*.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire littéraire sur un seul des passages.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d’examen est *[20 points]*.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario literario sobre un solo pasaje.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es *[20 puntos]*.


© International Baccalaureate Organization 2014

https://xtremepape.rs/

*ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ ስነጽሁፋዊ አስተያየት ስጥ(ስጭ)።*

**1.**

ሚች በዳንኪራ ሲሸኝ ለቅሶና ሙሾ ቀርቶ፤
ደንቆት ኖሮ ዶርዜ ሰፈር ተመልክቶ።
ተመሰጠና ብእረኛው፤
የዕውቀት አባት ባለቅኔው፤
በዋይታ በለቅሶ ፈንታ፤
ሞት ሲጨፍርበት በሳቅ በእልልታ፤
እንዲህ በሎ ዛተበት …
"የታባቱ ሞትም ይሙት!"
ባካችሁ ዘመዶቼ! ስሞት ሞትም አብሮኝ ይሙት፤
በሳቅ በደስታ ግደሉት፤
በሀሴት በእልልታ ውገሩት፤
ከአጥንቴ በታች ቅበሩት፤
እባካችሁ ዘመዶቼ ለሞት የልብ ልብ አትስጡት።
እንደዶርዜ ወንድሞቼ፤
በሳቅ ታጅቤ ኮርቼ፤
በዳንኪራ ሰበቃ በዘፈን ሆታ አንትቼ፤
በሰርጌ ብቀበር ሞቼ።
እፀድቅ ነበር ባትረሱ፤
በእምባ ውሌን ባታፈርሱ።
ይህ ነበር የባለቅኔው አደራ
ያኔ ዶርዜ ሰፈር ቆሞ፤
"የእኔም ሞት እንዲህ በእልልታ
በደመቀልኝ" ብሎ ተደምሞ።
የዚያ የጠቢብ ብዕር
በሞት ላይ ይህን እንዳልፈረደ፤
እነሆ እርሱም ዕጣ ደርሶት
ሚች ተባለ ወደማይቀረው ሄደ።
"ሞቴን በዕልልታ ውገሩት" አለን?
የአደራ ቃሉን ይዘን
ይሁን እሺ"ዕልል" እንበል
ዕልልታ ለማን ገዶ!
ግን እንዴት ዕልል ይባላል?
ስነ - ጽሁፍ ፀጋው ሲገፈፍ
ግንዱ ሲወድቅ ተንዶ?
እውን እልል ይባላል?
ስነ - ጽሁፍ ፀጋው ሲገፈፍ
ግንዱ ሲወድቅ ተንዶ
እውን እልል ይባላል?
የተውኔት የግጥሙ አለቃ
የታሪክ የቋንቋው ሊቅ
ከኪነ ጥበብ ሰፈር ጠፍቶ፤
እንደምን እምባ አይፈስለት



https://xtremepape.rs/

ዛሬ ያ ታላቅ ሰው ሞቶ??
ብዕር የጨበጠበት
ጣቱ ሲቀመጥ ታጥፎ፤
    አገር የሚያክል ሰው አጥታ
    ጥበብ ቆሌዋ ተገፎ!
    እንዴት ዕልል እንበል?

*ህሊና ተፈራ፣ እኛ ቁጥር 2*፣ (2011)።



https://xtremepape.rs/

**2.**

ጎንደር እንደፈካ አበባ በምትስቅበት በዚህ ዘመን አንድ አስደንጋጭ ወሬ መላ ከተማውን አሸበረው:: ከአንዲት አነስተኛ ቁልቢጥ ከምታህል መንደር የመነጨው ወሬ በድብቅ እንዲያዝ ንጉሱ ጥረት ቢያ ደርጉም የወሬው ምንጭ ግን ጅረት ሆኖ አገሩን ሁሉ አደረሰው:: ንጉሱ አቤቶ እያሱ ነጋሪት አስጎስ መው አዋጅ ቢያስነግሩም የህዝቡ ፍርሃት ሊሰክን አልቻለም::

አዋጅ ነጋሪው እንጥሉ ስኪወርድ ድረስ ይለፈልፍ ጀመር:: "…አዋጅ! አዋጅ! የሰማህ ላልሰማው አሰማ! ከጃንተከል ዋርካ ፊትለፊት፤ ከአደባባይ እየሱስ በስተመስዕ፤ ከቤተመንግስት በስተ ባህር ያለው፤ ቅጠሉ እንደአርቦጅ የሆነ፤ ግንዱ ጥቁር፤ በጋ ከክረምት ደርቆ የማያውቅ ዛፍ ይገኛል:: ከዚህ ዛፍ ስር ያረፈ ሁሉ አልተነሳም:: ጥላው ያረፈበት ሰውና እንስሳ ሕይወቱ አልተገኘም:: በዚህ የዛፍ ጥላ ተነክቶ የሞተ ብዙ ነውና ከዛፉ ጥላ ማንም ሰው እንዳያርፍ ሲሉ ጃንሆይ ተናግረዋል:: ኋላ አልሰማንም እንዳ ትሉ:: በግና ፍየል፤ አህያና ከብት ያላችሁ ሁሉ እንሰሶቻችሁን ወደዛፉ ጥላ እንዳይሄዱ አግዱ:: ደሮዎቻ ችሁንም ቢሆን ጠብቁ::"

ይህን ቀሳፊ ዛፍ ለማየት መላ ጎንደሬ ነቅሎ ወጣ:: ለገበያ የመጣው ሁሉ የዛፉን አስፈሪ ወሬ ይዞ ስለ ሄደ ከምፅዋ ስከአክሱም፤ ከቋራ እስከ ጎጃም ዛፉን ለማየት የመጡ ነበሩ:: ብዙም ለወሬ ጆሮ አይሰ ጡም የሚባሉት ደገኞች እንኳ ፈረሳቸውን ኰልኩለው መጥተዋል:: ዛፉ ነፋስ እንኳ የማያንቀሳቅሰው ይመስል በፀጥታ ችምችም ያለ ጥልቅ አረንጓዴ ቅጠሉን እንደአርበኛ አበጥሮ ቆሟል::በዙሪያው የወዳደቁ የእንስሳትና የአእዋፍ አስከሬኖች ይታያሉ::

"ይህ የክፉ ዘመን መጀመር ምልክት ነው" ይላል አንዱ::

"ታላቁ ፋሲል ረገሙን ይሆን? አቤቶሁን ዮሐንስን አስቀይመን ነበር? አቤቶ ኢያሱስ ቢሆኑ ቂም ይዘው ብን ይሆን" ይላል ሌላኛው::

በዚህ ሰሞን፤ ህዝቡ ዛፍ እንዲቆረጥለት አጥብቆ ስለጠየቀ ታላቁ ኢያሱ ከአያታቸው ከፋሲል ቤተመን ግስት ወጥተው ከጃንተከል ዋርካ ስር ለጉባዔ ተቀመጡ:: ስለዛፉ መቆረጥ ህዝቡና ሊቃውንቱ እንዲመ ክሩበት አደረጉ::

በዚህ ጉባዔ ላይ ታላቁን ባለቅኔ፤ ክፍለዮሐንስን ተከትለው አንድ ሽማግሌ ከወደ ደብረ ብርሃን ሥላሴ መጡ:: ባህታዊ ይመስል ፀጉራቸውን ያስረዘሙ ናቸው:: ከመናገራቸው በፊት ስለዛፉ የሚሰጠውን ፍርድ ይሰሙ ጀመር:: ባለቅኔው ክፍለዮሐንስ ግን በንጉሱ ፊት ስለዛፉ ቅኔ መወድስ ለመዝረፍ አስቦ መልሶ ተወው::

"ጃንሆይ!" አሉ አንድ ሌላ ሽማግሌ ከህዝቡ መሀል ኩታቸውን እያጣፉ:: "ይህ ዛፍ በጥላው ቢገለን እኛ ከጥላው ርቀን አለመሞት እንችላለን:: የዛፉ ጥላ ጠዋትና ማታ በፀሐይ አንፃር ስለሚረዝም መርዘም እስከሚችልበት ያለው መሬት ተለክቶ ታጥሮ መቀመጥ ይችል ይሆናል:: ነገር ግን ጃንሆይ፤ ይህ ዛፍ እዚህ ቆሞ አይቀርም:: ፍሬ አፍርቶ ፍሬውም በነፋስ ወይም በወፎች ከተበተነ አገር ያዳርሳል:: በዚህ ምክኛት ራሱን በአገራችን አራብቶ ይጨርሰናል:: በአለም የሚገኘን ህዝብና እንስሳን ሁሉ ሊፈጅ፤ ምድ ርንም ባዶዋን ሊያስቀር ይችላል:: ስለዚህ ጃንሆይ 'ሳይቃጠል በቅጠል' እንዲሉ ዛፉ ፍሬ ሳያፈራ ይቆ ረጥ ባይ ነኝ::" እጅ ነስተው ተቀመጡ::

ይስማእከ ወርቁ፣ *ራማቶሀራ*፣ (2010)::



https://xtremepape.rs/